## እግዚኦ በመአትከ ኢትቅስፈኒ በመቅሰፍትከ ኢትገሥጸኒ 24/8/2012

# ለኢትዮጲያ ኦ/ተ/ቤተክርስቲያን ተከታዮች ምእመናን በሙሉ

አድህነኒ እግዚኦ እስመ ኅልቀ ኄር ወውህደ ኅይማኖት እምእጓለ እመሕያው መዝ11

አቤቱ አድነኝ ደግ ሰው አልቁዋልና ከሰው ልጆችም መተማመን ጎድሎአልና

እግዚአብሂእር አምላክ ሰውን በራሱ መልክ ከፈጠረው በኃላ ማመን እና መተማመን በመጥፋቱ እግዚአብሂእርና ሰው እንዴት እንደተራራቁ የሚያሳየን ቅዱስ መጽሐፍ ነው ከሚኖርበት ከክብር ቦታ ወርዶ የሞት ሞት የመጣበትን አካሄድ የሄደው የሚታመነውን አምላኩን ባለማመኑ የማይታመነውን በማመኑ ውድቀቱን በመጸሐፉ ቁልጭ አድርጎ ያሳየናል ዛሬ ሀገራችን ኢትዮጲያ በአለም ላይ ከነበራት ክብር ወርዳ ልጆቹዋ በሚያከብሩን ህዝቦች ዘንድ ተዋርደን መግቢያ መጠጊያ በማጣት እየተቅበዘበዝን ያለንበት ዘመን ምክንያቱ እና መንስኤው አመጽ ያመጣው ችግር ነው አባቶቻችን በአባቶቻቸው ህግና ስራት ላይ በማመጻቸው የኢትዮጲያ ኦ/ተ/ቤተክርስቲያን በረዥም ዘመን ታሪኩዋ ታይቶ ወደማይታወቅ ጎዳን ተጉዛ ቤተክርስቲያኑአን 4 ቦታ ከፍሎአት እንገኛአለን ሰው ሀጢያተኛ ባህርይ ስላለውና በዚህም ምክንያት ለእግዚአብሄር ያለውን ፍቅርና እቅድ ሊለምድ ባለመቻሉ ከእግዚአብሄር ሲለይ ያሳያል ሰው ባፈጣጠሩ የእግዚአብሂር የቅርብ ወዳጅ እንዲሆን ተፈጥሮ ነበር ነገር ግን ሰው የገዛ መንገዱን በመከተሉ ከእግዚአብሂር ጋር ያለው ግንኙነት ተቁአረጠ። እነዛ ደጋግ አባቶቻችን የራሳቸውን ቤተክርስቲያን ለማስተዳደር እግዚአብሄር አልፈቀደላችሁም በማለት የኮብት ቤተክርስቲያን ስር በእምነት በመቆያታቸው ባለማወቅ አስመስሎባቸው ለ1600 ዘመን በኮብቶች ቤተክርስቲያን ስር ቆይተው በግፈኛው የሞሶሎኒ ወረራ ምክንያት በሃገሪቱና በህዝቡ ላይ የተደቀነውም መከራን በደል እምቢኝ በማለት ህዝባቸውን ከግፍ ወረራ ለማላቀቅ ብጹ ወቅዱስ አቡነ ጲጥሮስና ብጹ ወቅዱስ አቡነ ሚካኤል በግንባር ቀደምትነት ለቤተክርስቲያናቸውና ለሃገራቸው መስዋት ሆነው ሲሰዉ የግብጹ ጳጳስ አቡነ ቄርሎስ በጵጵስናቸው ላይ ተቀምጠው ይህንን በህዝብና በመንፈሳዊ አባቶች ጭፍጨፋ እና ቤተክርስቲያናት በእሳት ሲነዱ ቸለል በማለታቸው የኢትዮጲያ ቤተክርስቲያን በወሰደችው አቁአም ላንዴና ለመጨረሻ ከኮፕት ቤተክርስቲያን ተላቃ በራሱዋ ልጆች መተዳደር የጀመረችበት ምክንያት በቤተክርስቲያንና በህዝብ ላይ በደረሰ በደል ነበር ዛሬ በቤተክርስቲያንና በሃገር ላይ ችግር አልደረሰም እንላለን በህዝቦችና በመንፈሳዊ አባቶች ላይ መከራ አልወረደባቸውም እንላለን መቼ ነው በቤተክርስቲያኑዋ ላይ በደረሰው ችግር የምናለቅሰው እና የምናዝነው መቼ ነው በጋራ ቆመን ወደአምላካችን ስለህዝባችን እና ስለሀገራችን እጆቻችንን ዘርግተን ወደ አምላካችን የምንጮህው ተመስሉ ኪያየ በከመ እነ እትሜስሉ ለክርስቶስ እኔ ክርስቶስን እንደመሰልኩ እናንተም እኔን ምሰሉ እንዳለው ቅዱስ ጳውሎስ የቤተክርስቲያን አገልጋዮች እንዲሁም ሀገራችንን እናድናለን የሚሉ የፖለቲካ ፓርቲዎች እኛ እንደማንስማማ እናንተም አትስማሙ ብለውን የኢትዮጲያ ልጆች የመግባቢያ ቁአንቁአችን ጠፍቶ ለቤተክርስቲያንም ሆነ ለሃገርና ለህዝብ መድረስ አቅቶን ተበታትነን የኢትይፐጲያ ሰቆቃና ጥፋት እንኩአን አላገናኝ ብሎን 21 አመት አስቆጠርን መጽ/ሲራክ ኢታአብሰ ለሰብአ ሀገርከ ወኢታስህት ርእሰከ በማእከለ ህዝብ አገርና ህዝብህን በድለህ እትዝብት ላይ እንዳትወድቅ ተጠንቀቅ ቅድስት ቤተክርስቲያናችን በታሪኩዋ ትምህርቱዋ እንዳይጣመም ለትምህርቱዋ ሰትጠነቀቅ ኖራለች የቁስ አርዮስ ትምህርት ሁለት ጳጳሳትን ማለትም ተፍጻሜተ ጴጥሮስንና እለ እስክንድሮስን በጉዳዩ ጣልቃ እንዲገቡ በእስክንድርያ 100 ጳጳሳት ከእስክንድርያ ከሊቢያ እና ከሌሎችም ሀገሮች እንዲሰበሰቡ አድርጉዋል እንዲሁም በ325ዓ/ም በኒቅያ ከአለም ዙሪያ በመጡ 318 ጳጳሳት ጉባኤ ተደርጎአል ይህ ሁሉ የተፈጠረው በአንድ ቄስ በተሳሳተ

ትምህርት ነበር የትምህርቱ መስፋፋት መጥፎ ስለነበር ማንም እግዚአብሄር ይጠይቀው ተውት ያለ አልነበረም የመጀመሪያ የቤተክርስቲያን መከፋፈል በክርስቶስ ባህርይ ትምህርት ምክንያት በ450ዓ/ም ተከሰተ ሌላው መከፋፈል በ11 መቶ ክፍለ ዘመን በካቶሊክና በሮማን ኦርቶዶክስ መካከል በስርፀተ መንፈስ ቅዱስ ትምህርት መለያየት ሲሆን 3ኛውና ትልቁ መከፋፈል በ15ኛው መ/ክ የተቀዋሚዎቹ መሪ በሆነው በሉተር ምክንያት የተለያዩ ባህለ ሀይማኖቶች ተፈጠሩ ሰዎች የራሳቸውን አስተሳሰብ ማራመድ ሲሆን ዛሬም የቤተክርስቲያናችን ችግር ይህንን ያካተተ መሆኑን ከአባቶቻችን ህግና ስራት መፋለስ ከምን መጣ 4ኛው የኢ.ተ.ቤ ፓትሪያርክ ብጹ ወቅዱስ አቡነ መርቆሪዎስ በግፍ ከውንበራቸው ተገፍተው ሲባረሩ ገዢው ፓርቲ TPLF የአማራን ሕዝብ በጠላትነት ፈርጆ የተነሳበት እና በኢትዮጲያ ኦ፣ተ.ቤተክስቲያን እንዴት እናዳክማት በሚል ትግል በመሆኑ አነሳሳቸው የቤተክርስቲያኑም አባት ወንጀላቸው ከአማአራ ህዝብ መፈጠራቸው ሲሆን ለስደት ተዳርገው በስደት እንዲኖሩ ተገደዋል በቦታቸው በህይወት ያለፉት አባ ጳውሎስ 5ኛው የቤተክርስቲያኑዋ መሪ ሆነው የተሾሙበት ሚስጥርም ለግዢው ክፍል አመቺነት በመፈለጋቸው ትውልዳቸውም ቀዬአቸውም ግምት ውስጥ ገብቶ ቤተክርስቲያኑአን ለማድከም ጠቃሚ ሰዎች ተብለው ከተመረጡት አንዱ በመሆናቸው ነበር ዛሬ አባ ጳውሎስ በህየወት አልፈዋል ነብሳቸውን ይማር እላለሁ ዛሬ አስከሬን ፍታት ላይ በውጭ ያሉ ቤተክርስቲያን ውስጥ አወዛጋቢ ሆኖ እየሰማን ያለንበት ሰአት ነው ዛሬ በእግዚአብሄር መንግስት ገብቶ እንደመፍረድ ስለሚያስቆጥር ይፈታ አይፈታ የሚያወዛግብ አልመሰለኝም በርግጥ አባ ጳውሎስ አስከሬን ፍታት ብቻ አይደለም ተቃዋሚ ያሉትን በሚያስተዳድሩት መሪት ላይ እንዳይቀበር ትዛዝ የሚሰጡ ደንዳና ለብ የነበራቸው ሰው እንደነበሩ አንድ ሁለት ምሳሌ ልጥቀስ አንድ የቤተክርስቲያን አባት ማረጋቸውን ባልሳሳት መምህር ሀይለማሪያም ያአባ ጳውሎስን አስተዳደር ተቃውመው ጠቅላይ ሚንስትሩ ድረስ ይደርሳሉ በዚህ መሀል 15 አመት እድሜ ያለው ልጃቸው ያርፋል ከ1 ሳምንት በላይ በየትኛውም ደብር እንዳይቀበር ከልክለው አስከሬን ይዘው አዲስ አበባ አቅቶአቸው ወደ ተውልድ ሀገራቸው ትግራይ ድረስ ይዘው ሄደው ተከልክለው በጠቅላይ ሚንስትሩ አማላጅነት እንደተቀበረ አውቃለሁ በአሜሪካ ሀገር ኮሎምቦስ ቅዱስ ዮሴፍ ቤተክርስቲያን የተቀበሩት የ 80 አመት እድሜ ባለጸጋ አባ ሲሳይ እየሩሳሌም እንዳይቀበሩ ታግደው ነበር በዛው በአሜሪካ የተቀበሩት ።እኔ ግን ዛሬ ይሄ ጭካኔ ይደገም የሚል ፍላጎት የለኝም የወደቀ አንሱ የሞተ ቅበሩ ይላሉ ያገሬ ሰዎች ዛሬ መነጋገሪያው እግዚአብሄር እየሰራው ያለው ስራ አለ የህን ሰራ ማገዝ እያንዳንዱ የተዋህዶ ልጅ የሚጠበቅበት ቤተክርስቲያናችንን ወደ አንድነት ለማምጣት የኢትዮጲያ ኦ.ተ.ቤ ልጆች ተቀራርቦ መነጋገሪያችን ሰአት ዛሬ ነው ለቤተክርስቲያናችን አንድነት በር መክፈቻው ተቀዳሚ መሆን ያለበት አላግባብ በመንግስት ጫና ከወንበራቸው የተነሱትን አባታችን ብጹ ወቅዱስ አቡነ መርቆሪዮስ ወደ ወንበራቸው ለመመለስ ምእመኑ በአንድነት መቆም አለበት በርግጥ እንቅፋት አለው እንቅፋቱም ቤተክርስቲያኑዋ የተወሳሰበ ችግር ውስጥ ነች 2004 በአዲስ አበባው ሲኖዶስ ላይ የተነሳው
1ኛ/አባ ጳውሎስን ቅድስት ድንግል ማርያም ንጽሐ ጠባይ አልነበራትም ብለው መመረቂያ ጽሁፍ ላይ ጽፈዋል።ይሄ የሀይማኖት ጉዳይ ስለሆነ መልስ ይስጡን? በማለት ሲኖዶሱ የጠየቀ ቢሆንም ፓትሪያርኩም የመመረቂያ ጽሁፌ ኮፒ ተደርጎ ይሰጠኝና ተዘጋጅቼ ነው መልስ የምሰጠው በማለት የፌዝ ንግግር በመናገር እንደቀላል ታልፉአል ቀደም ብሎም ሊቀ ሊቃውንት አያሌው ታምሩ ገበያ ላይ የዋለውን የአባ ጳውሎስ መጽሀፍ በፍጹም አንድ የኢ/ኦ/ተ/ቤ አባት ይህን መጽሀፍ ሊያሰራጭ አይችልም የመቤታችን ክብርና የስላሴን አንድነት ይጻረራል በማለት አሳግደዋል አባ ጳውሎስም በዚህ ላይም ቤተክርስቲያንን ይቅርታ አልጠየቁም ወይም

አላስተባበሉም በዝምታ የታለፈ ጉዳይ ነበር ዛሬ በዚሁ 2004 ሲኖዶስ ስብሰባ ላይ በቢተክርስቲያኑዋ ውስጥ ስም ዝርዝር እየተጠቀሰ በሀይማኖታቸው እጸጽ ተገኝቱአል የተባሉ ሰዎች ከምነጋገር ውጭ እስካሁን ሰአቱም ከሃላፊነታቸው ያልተነሱም እስካሁን ይገኛሉ  በገዳማት መፍረስ ላይ አንድ አይደለም በርካቶች ጳጳሳት ለምን ገዳሙ እንዲፈርስ አንድ ሆኑ ቤተክርስቲያን ከነሙሉ ሀብቱዋ ሲወድም አንድ ሰው ለምን ተጠያቂ ሆኖ አልቀረበም ከብዙ በጥቂቱ 700 ዘን ያስቆጠረው ቅድስት ሀና ገዳም በደብረ ማርቆስ ጣና ሀይቅ ላይ የውደመው ቤተክርስቲያን  ጎንደር ስላሴ እድሜ ጠገቡ የቅኔ ትምህርት ቤት የዝቁዋላ እና ያሰቦት ገዳም ደን ማን ተጠያቂ ሆነ ይህ ሁሉ ሀበቱዋ ሲወድም መመን አብረው ሲታረዱ  ቤተክርስቲያኑዋ ዝምታስ ከምን መጣ የሄ ደግሞ በአንድ ሰው የሚሰራ አይደለም ለጥቅምና ለስልጣን ከአኮበኮበው ውጭ በቤቱዋ ዲቃላ ገብቱአል ዲቃላ ማለት የኛ ያልሆነ ግን የኛን የሚመስል  የኛ ያልሆኑ አባቶች ግን የኛን አባቶች የሚመስሉ በርክተዋል

የተዋህዶ ልጆች በሉ ጎንበስ ቀና
ጉዳችሁ ጀመረ መቼ  አበቃና
እግዚኦ ማለት ያሻል ተሰባሰቡና

ወርቅ አልማዙ ሄዶ ሁአላ እንዳንቀር ወና  ስለዚህ ይህን በቤተክርስቲያን ላይ የተጋረጠ ችግር በአንድነት ካልሆነ አይፈታም በሀገር ቤት ያሉ አባቶች የእግዚአብሄርን ሰራ እንዳያደናቅፉ ሌላ ፓትሪአርክ ሾመው ወደሌላ ስህተት እንዳይገቡ እና ለመከራችን መርዘም ምክንያት እንዳይሆኑ በአንድ ላይ ቆሞ አቤት ማለት ተገቢ ነው። ዛሬ የተዋህዶ ለጆች የናፈቀን የቤተክርስቲያኑአ አንድነት እንጂ አዲስ ፓትሪያርክ አይደለም በውጭም ያለነው በየደብራችን አባቶቻችንን ማስጫነቅ ይጠበቅብናል እንድሙስሊም ወንድሞቻችን  ምርጫችን አንድነታችን  እያልን መጮህ የጠበቅብናል ምርጫችን ዘራችን ሳይሆን ምርጫችን ቤተክርስቲያናችን ይሁን ይህን በማድረጋችን በርግጥ ምኞታችን አንድነት ከሆነ ሩቅ አይደለም የእግዚአብሄር የምህረት አይኖችም ወደኛ ይሆናሉ ለዚህም ስራ መቃናት በቤተክርስቲያን በኩል የሚታወቁ በሃይማኖት ጥንካሪ ያላቸው ቅን ቅን በወዳጆቻቸው የሚከበሩ የተዋህዶ ላጆች ሁሉ በአውሮፓም በአሜሪካም በአውስትራሊያም በ አፍሪካም እይተሰባሰቡ ተወያይቶ በየአካባቢው ሰብሳቢ መርጦ የተዋህዶን ልጆች ማወያየት ተገቢ ነው ይህንንም  ሃሳብ ለጊዚያዊ ጥቅም የቆሙ አገልጋዮች አንድነቱአን  ላይፈልጉ የሚችሉ ይኖራሉ ይህንንም መረዳት ያስፈልጋል ለእውነት መቆም የማይቻልበት ዘመን ይህ የኛ ዘመን ነው ከማስገደል አንስቶ ከማህበረሰቡ  ያስገልላል ስም ያስወጣል ሰሚ ማጣት ሁሉ አለው ግን አንድ ነገር ገን ማወቅ አለብን እርሱም የቆምኩት ለምንድን ነው በሎ እራስን መጠየቅ ነው መስዋትነቱ ከበድ ያለ ነው ይህን መቀበል በቻ ነው ።

ለሁሉም የእግዚአበሄር አምላክ እርዳታ አይለየን ደህና እንክረም

እግዚአብሄር አምላክ ኢትዮጲያን ከጥፋት ይጠብቅልን
የተዋህዶ ሀይማኖትንም አንድነቱዋን ይመልስልን
ወንድወሰን ሰብሰቤ ከሀገረ እንግሊዝ ተጻፈ
covkidanemheret@yahoo.co.uk